

# በሌላ ቦታ ላይ መወለድ?

በውቅና-አልባ አገር (ዲፋክቶ ስቴት) ውስጥ ለሚኖሩ ህፃናት አካታች
አለም አቀፍ የመብት ጥበቃን አውን ማድረግ

## ዋነኛ ማጠቃለያ

### የሪፖርቱ አላማዎች

ሰባአዊ መብቶች ሁሉን አቀፍ ናቸው ብለን እንውሰድ። እናም በመላው አለም ያሉ ህፃናት ያለብሄር፥ ቋንቋና ዘር ልዩነት እነዚህ መብቶችህ አሏቸው አንበል። እንደዚያም ሆኖ በአንድ ምድብ ያሉ ህፃናት ስርአታዊ በሆነ መንገድ ከአለም አቀፍ ህግ ጥበቃ ተገልለዋል። እነዚህም **አውቅና- አልባ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ህፃናት** ናቸው። ይህ ሪፖርት ለአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ስለነዚህ ህፃናት መገለል መረጃ ይሰጣል፥ እነዚህ ህፃናት እንዴት መጠቃለል እንዳለባቸው ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል።

### የሪፖርቱ ፀሃፊዎች

የማስትሪችት ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድንና አአአ በ2024 “በአውቅና-አልባ አገሮች የሚገኙ ህፃናት የማደግ መብቶችን አውን ማድረግ” በሚል ርአስ የተካሄደው የዩኒቨርሲቲው አለማቀፍ ኮንፈረንስ ተሳአፊዎች ናችው።

### አውቅና አልባ አገር ምንድን ነው?

አውቅና አልባ አገሮች አገር ለመሆን የሚያስፈልጉ አራት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የፖለቲካ ስሪቶች ናቸው(1933 አኤአ ሞንቶቪዲዮ ኮንቬንሽን)። እነዚህም፥ ቋሚ ህዝብ፣ የታወቀ ሏአላዊ መሬት፣ መንግስትና ከሌሎች አገሮች ጋር ግንኙነት የማድረግ አቅም ያላቸው ሆነው ነፃነታቸውን አውጀው ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት አባል ያልሆኑ ናችው። ባሁኑ ሰአትም ኮሶቮ፣ ሶማሊላንድና የሰሜን ቆጵሮስ ቱርክ ሪፓብሊክ ይገኙበታል።ባጠቃላይ ወደ ዘጠኝ ሚሊዮን የሚሆኑ ህፃናትን የሚያካትቱ ናቸው።

### ችግሩ

ከፍልስጤም በስተቀር በውቅና አልባ አገሮች የሚኖሩ ህፃናት መብቶች በተባበሩት መንግስታትም ይሁን በስሩ ያሉ ማናቸውም ድርጅቶች ክትትል አይደረግባቸውም። አውቅና አልባ አገሮችም ቢሆኑ ለማንኛውም የተመድ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ሪፖርት አያደርጉም። አግባብነት ያላቸው መንግስታዊም ይሁኑ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትም እንዲሁ ሪፖርት አያቀርቡም። በዚህም ምክንያት የህፃናት መብቶች ያለተጠያቂነት ይጋሰሳሉ።

ጀርባ ላይ ተጨማሪ ያንብቡ >

## የመፍትሄ ምክረ ሃሳቦች

በውቅና አልባ አገሮች ስር ያሉ ህፃናት ሙሉ አውቅና ባላቸው አገሮች ውስጥ ካሉ ህፃናት ጋር እኩል ከለላ አለማግኘታቸው ተቀባይነት የለውም። ይህ አውንአታ በአይምሮአችን ይዘን አውቅና አልባ አገሮች አስካሉ ድረስና ከመኖራቸው ጋር የተያያዘ ግጭት አስካልተፈቱ ድረስ የሚከተሉትን መፍትሄዎች አናቀርባለን፥

**1** **የተባበሩት መንግስታት ብውቅና አልባ አገሮች ላይ የህፃናት መብት ጉዳይ ወይም የህፃናት መብትን ጨምሮ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ልዩ ራፖርተር ይሹም።**

**2** **አውቅና አልባ አገሮች በተባበሩት መንግስታት የህፃናት መብቶች ክትትልና ረፖርት የማድረግ ስራ ውስጥ እንዲጠቃለሉ ማድረግ።** ሁለት አማራጭ አካሄዶች እንደተመራጭነታቸው ዘርዝረናል።

**a.** **አውቅና የለሽ ሃገራት የተመድ ህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን እንዲፈርሙና እንዲያፀድቁ መጋበዝ።** አሁን ባለው ሁኔታ ይህ አማራጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህን እንዲያደርጉ ህግ ይፈቅድላቸዋል። ይሄን አውን ለማድረግ ሁለት ተግባራዊ መንገዶች አሉ፥

**i.** በተመድ ጠቅላላ ስብሰባ በኩል የተመድ ህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን እንዲያፀድቁ መጋበዝ።

**ii.** በተመድ ጠቅላላ ስብሰባ በኩል እንደ ፍልስጤምና ቫቲካን "አባል ያልሆኑ ታዛቢ አገሮች" ሆነው የተመድ ህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን እንዲፈርሙና እንዲያፀድቁ መጋበዝ።

**b.** **ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው አገራት በሪፖርታቸው ላይ አውቅና አልባ በሆኑ አገራት የሚገኙ ህፃናት መብቶችን ጉዳይ እንዲጨምሩ መጋበዝ።** ተመራጭ የሚሆነው አውቅና አልባ አገሩ ራሱን በቻለ ክፍል ወይም በቅጣይ(አኔክስ) መልክ አውቅና ባለው አገር ሪፖርት ላይ ቢጨመር ነው።

**3** **የተለያዩ የተመድ ሰአብአዊ መብት አካላት አውቅና አልባ አገሮችን በዘላቂነት በእኩል አይን የሚያስተናግዱበትን አካሄድ መፍጠር።**

**4** **መልአክት ማስተላለፍ፥** ሁሉም ህፃናት መብቶች እንዳሉዋቸውና በውቅና አልባ አገሮች የሚኖሩ ህፃናት መብቶች ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን የሚያረጋግጥ የአቋም መግለጫ ማውጣት።

Children's Rights Research

**Maastricht University**
**Faculty of Law**
Bouillonstraat 1-3
6211 LH Maastricht
The Netherlands

childrensrights@maastrichtuniversity.nl
childrensrightsresearch.com
Powered by MV80.nl

childrightsresearch
childright1410
ResearchOnChildrensRights